## መልመጃ አንድ፥ ተዋንያን
**Exercise One: Actors**

1. ይህ ኪነት የተከናወነው የት ነው?
2. በዚህ ኪነት ውስጥ ስንት ተዋንያን ተሳትፈዋል?
3. ውቤ ማን ናት?
4. እሌኒና ወ/ሮ ውቤ ምን ዓይነት ዝምድና አላቸው?
5. ሲጋራ የሚያጨሰው ማን ነው?
6. በጀርባው ተኝቶ ፊልም የሚመለከተው ማን ነው?
7. አቶ ዘሪሁን የለበሱት ልብስ ምን ዓይነት  ነው?
8. መጽሐፍ ያነብ የነበረው ማን ነው?
9. የሮዛ ጥፋት ምን ነበር?
10. የቤተሰቡ አስተያየት ምን ይመስላል?

## መልመጃ ሁለት፥ምንባብ ፥ትክክለኛውን መልስ ከ ሀ፥ ለ እና ሐ  ምረጡ
**Exercise Two: Reading Comprehension. Choose the right answer between A, B, and C.**

1. ከሰል ምድጃ

ሀ. እሳት ማንደጃ ነው

ለ. ውሃ ማሞቂያ ነው

ሐ. ከሰል የሚነድበት ነው

2. መዞ ማውጣት

ሀ. መሳብ

ለ. ለይቶ ማውጣት

ሐ. መደባለቅ

3. ከመዳፏ ፈልቅቃ አወጣች

ሀ. ከደረቷ ላይ አስቀመጠች

ለ. በእጇ ያዘች

ሐ. ከእጇ አላቀቀች

4. የሲጋራ መለኮሻ

ሀ. ሲጋራ ማስቀመጫ

ለ. ሲጋራ መያዣ

ሐ. ሲጋራ ማቀጣጠያ

5. ሥራዋን አቋረጠች

ሀ. ሥራዋን አቆመች

ለ. ሥራዋን ጀመረች

ሐ. መልሱ አልተሰጠም

6. የቴሌቪዥን መቆጣጠሪያ

ሀ. የቴሌቪዥን ገመድ

ለ. የቴሌቪዥን ማስቀመጫ

ሐ. የቴሌቪዥን ማብሪያና ማጥፊያ

7. መሸጋገሪያ ማለት

ሀ. መተላለፊያ

ለ. መረማመጃ

ሐ. ሁለቱም ትክክል ናቸው

8. ኪሱ ውስጥ ፍርፋሪ ተገኘ

ሀ. ኪሱ ውስጥ ብር ተገኘ

ለ. ኪሱ ውስጥ ሣንቲሞች ተገኙ

ሐ. ኪሱ ውስጥ ቀሪ/ትራፊ ተገኘ

9. በወቅቱ መገሰጽ

ሀ. በጊዜዉ፡ መቆጣት

ለ. በጊዜው ማረም/ማስተካከል

ሐ. ሁለቱም ትክክል ናቸው

10. ጥቅሙን ማስረዳት

ሀ. የሚያመጣውን ውጤት መንገር

ለ. ጉዳቱንና ጤናማ ጎኑን መግለጽ

ሐ. ሁለቱም ትክክል ናቸው

## <u>መልመጃ ሦስት፥ በክፍል ሀ ያሉትን ቃላት ወይም አባባሎች ከክፍል ለ ጋር አዛምዱ</u>

**Exercise Three: Match these words or expressions in column A with their equivalent in column B.**

| አምድ ሀ<br>**Column A** | አምድ ለ<br>**Column B** |
| --- | --- |
| 1. ፍርፋሪ | ሀ. አለማመን |
| 2. በወቅቱ | ለ. መቀበል |
| 3. ጉዳት | ሐ. ማጨስ |
| 4. ጥቅም | መ. መምከር |
| 5. ማስረዳት | ሠ. ምግብ ተበልቶ የተረፈ |
| 6. መውቀስ | ረ. አደጋ |
| 7. ማቡነን | ሰ. የሚያስፈልግ |
| 8. ማመን | ሸ. መግለጽ |
| 9. መካድ | ቀ. በጊዜው |
| 10. ድንጋጤ | በ. አለመረጋገት |

## <u>መልመጃ አራት፥ በመዝገበ ቃላት ውስጥ ያሉትን ቃላት በመጠቀም ክፍት ቦታዎችን ሙሉ</u>

**Exercise Four: Fill in the blanks by using words from the glossary**

1. ሮቤል _________ ብሎ እማዬ ይሄን ያህል ለምን ታካብጃለሽ? አለ።
2. ዘሪሁን ሮቤልን _________ ተቆጣ።
3. ይሄ ከየመንገዱ ላይ እና ከዚህ ከየቪዲዮው _________ ቋንቋዎችህን ተዋቸው።
4. ከእኛ ከወላጆችህ ጋር የምትነጋገር ስለ መሆንህ አስተውለውና_________ እንነጋገር።
5. ሮቤል ፀጉሩን_________ ቆፈረ።
6. ሮዛ ሮበል ሲናገር_________ ።
7. ከጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን የሲጋራ _________ አነሳች።
8. በወቅቱ ያየሁትን ባለመናገሬ እራሴን እንደ _________ እቆጥራለሁ።
9. ከኪሱ ውስጥ የሲጋራ_________አግኝቻለሁ።
10. ዘሪሁን – በድንጋጤ ቁጣ ሮዛ ላይ_________ ።

## መልመጃ አምስት፥ የተሰመሩትን ቃላት በተመለከተ ጥያቄዎች ጠይቁ

**Exercise Five: Ask questions corresponding to the underlined words**

1. ሲጋራ መለኮሻ
2. ፀጉር መፈልቀቅ
3. መጻፍ
4. ዓይን ለዓይን መገጣጠም
5. መርበትበት
6. አጋጣሚ
7. ግራ መጋባት
8. ማጎንበስ
9. ማቃናት
10. ቴሌቪዥን አስክሪን

## መልመጃ ስድስት፥የማዳመጥ ምንባብ፥ ውይይቱን ተመልከቱና በእያንዳንዱ መሥመር ላይ ያላችሁን አስተያየት ስጡ፡፡

**Exercise Six: Listening comprehension. Watch the conversation and comment each line**

ሮቤል – ኮስተር ብሎ እማዬ ይሄን ያህል ለምን ታካብጃለሽ?

ዘሪሁን – ቆጣ ብሎ – – ሮቤል! በመጀመሪያ ይሄ ከየመንገዱ ላይ እና ከዚህ ከየቪዲዮው የምትለቃቅማቸውን ቋንቋዎችህን ተዋቸውና ከእኛ ከወላጆችህ ጋር የምትነጋገር ስለ መሆንህ አስተውለውና በአማርኛ እንነጋገር፡፡

ሮቤል – ፀጉሩን በጣቶቹ እየቆፈረ -- ኧ–ረ–አ–ባ– እ–ኔ እ–ኔ እኮ

ሮዛ – አቋርጣው ከፊት ለፊታቸው ካለው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን የሲጋራ መለኮሻ እየጠቆመች እና ለምን ይሄንን ነገር ያዝከው ብለን መጠየቅ አልነበረብንም፡፡

ሮቤል – እ–ህ ቆይ ግን እላዩ ላይ ያለውን ባትሪ ይታያችኋል?

ዘሪሁን – ብናየውም ሮቤል ለባትሪው ባትሪ ብቻ አለመያዙን ልቦናው ያውቃል፡፡

ሮዛ – አዎን በዚያ ላይ በወቅቱ ያየሁትን ባለመናገሬ እራሴን እንደ ጥፋተኛ ልቁጠረውና ከዚህ በፊትም ያንን ነጩን ሸሚዝህን በማጥብበት ሰዓት ከኪሱ ውስጥ የሲጋራ ፍርፋሪዎችን እንዳገኘሁኝ እነግርሃለሁ፡፡

ዘሪሁን – በድንጋጤ ቁጣ ሮዛ ላይ እያፈጠጠ –ምን!?

ሮቤል – ደንግጦ በመቃወም ኧረ አባዬ …

## <u>መልመጃ ሰባት፥ አዎንታ ወይም አሉታ ጥያቄዎች</u>

**Exercise Seven: yes or no questions**

| | አዎን | አይደለም |
|---|---|---|
| 1. ትዕይንቱ የሚጀምረው ከቤቱ በረንዳ ላይ ነው | | |
| 2. የአቶ ዘሪሁን መኖሪያ ቤት ትዕይንቱ ተከናወነበት | | |
| 3. ውቤ የቤት ሠራተኛ አይደለችም | | |
| 4. ሲጋራ የሚያጨሰው ሮቤል ነው | | |
| 5. እሌኒ የሮቤል አክስት ናት | | |
| 6. አቶ ዘሪሁንና ወ/ሮ ሮዛ ባልና ሚስት ናቸው | | |
| 7. ትዕይንት አራት የተከናወነው ምግብ ቤት ነው | | |
| 8. የሲጋራ መለኮሻው የተገኘው ሮዛ ኪስ ውስጥ ነው | | |
| 9. ሮዛ ጥፋተኛ መሆኗን አምናለች | | |
| 10. አቶ ዘሪሁን ሮዛን ተቃውመዋል | | |

## <u>መልመጃ ስምንት፥ ተቃራኒ የሆኑትን ቃላት በመልመጃው ውስጥ ፈልጉ</u>

**Exercise Eight: Find the antonyms of these words in the text.**

1. ማክበድ
2. ማስተዋል
3. በወቅቱ
4. መገሰጽ
5. ጥቅም
6. መውቀስ
7. መካድ
8. ማስወገድ
9. ማጎንበስ
10. መጽሐፍ ማጠፍ

## <u>መልመጃ ዘጠኝ፥ ውይይቱን በራሳችሁ አባባል/ቃላት አሳጥራችሁ ጻፉ</u>

**Exercise Nine: Summarize the dialogue in your own words.**

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

___________________________________________________________

## <u>መልመጃ አስር፥ ኪነት መሥራት፡፡ ኪነቱን ተለማምዳችሁ የከተማውን አማርኛ በመጠቀም ዝግጅት አቅርቡ፡፡ ይህ ዝግጅት ባህሉን፥ አቀረራረቡን እና ሌሎች የቋንቋው ስልቶች እንዲገቡ ያስፈልጋል፡፡</u>

**Exercise Ten: Role play:** Rehearse and perform the skit by using urban Amharic.

Be mindful to reflect the local culture, gestures and other kinesics aspects of language